## የመንግሥት ቦንድ ምንድር ነው?

የመንግስት ቦንድ በዋናነት በአገሪቱ ገንዘብ መንግሥት የሚያካሂዳቸውን ፕሮጀክቶች ወይም ሌሎች ወጪዎችን ለመሸፈን ከዜጎቹ ወይም ከሌሎች ኢንቨስተሮች ገንዘብ ለማሰባሰብ የሚወጣ ቦንድ ወይም የሚበደርበት መንገድ ነው::ስለዚህ ቦንድ ማለት አንድ ኢንቨስተር የተወሰነ መጠን ያለው ገንዘብ ለተወሰነ ጊዜ በተቀመጠለት ወለድ መጠን ለመንግሥት የሚያበድርበት የውል ሰነድ ነው::መንግሥት ገንዘብ በውጭ ምንዛሪ ለማሰባሰብ የሚያወጣው ቦንድ ደግሞ ሉዐላዊ ቦንድ (Sovereign Bond) ተብሎ ይታወቃል::ሌላው ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ በየጊዜው እየቆጠቡ ለኢንቨስትመንትና ለልማት የሚውል የሀብት ክምችት መፍጠር ባልቻሉ ጊዜ መንግሥት ይህንን ልማታዊ ዓላማ ለማበረታታት ከፍ ባለ የወለድ መጠን ቦንድ በመሸጥ ዜጎች የሚቆጥቡበትን መንገድ ያመቻቻል:: የዚህ ዓይነት ቦንድ የቁጠባ ቦንድ ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን ይህም የአገር ውስጥ ቁጠባን ለማበረታታት በገበያ ላይ ይገኛል::

በታሪክ ቦንድ መሸጥ የጀመረችው እንግሊዝ ስትሆን በ1693 ከፈረንሳይ ጋር ላካሄደችው ጦርነት ገንዘብ ለማሰባሰብ የመጀመሪያውን ቦንድ ለህዝብ በማቅረብ ተጠቅማለች:: በኋላም የተለያዩ የአውሮፓ መንግሥታት የጊዜ ገደብ የሌለው ቦንድ/Perpetual Bonds/ እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ድረስ እያወጡ ሲሸጡ ቆይተዋል::በአሁኑ ጊዜ የጊዜ ገደብ የሌለው ቦንድ/Perpetual Bonds/ የሚያሰራጭ አገር የለም:: በአጠቃላይ መንግሥታት ለኢንቨስትመንት እና ሌሎች የሥራ ማስኬጃ ወጪዎችን ለመሸፈን እንዲሁም የአገር ውስጥ ቁጠባን ለማበረታታት ቦንድ እያወጡ እንደሚሸጡ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ:: ይህ አሰራር በዚህ ባለንበት ዘመንም ያለ ነው::

የመንግሥት ቦንድ አስተማማኝና ከስጋት ነፃ / Risk Free/ በመሆኑ ይታወቃል:: ምክንያቱም መንግሥት የቦንድ መክፈያ ጊዜ በሚደርስበት ጊዜ ከታክስ፣ከግብርና ከሌሎች ምንጮች ገንዘብ በማዘጋጀት ግዴታውን የመወጣት ብቃት ስላለው ነው::ስለዚህ በመንግሥት ቦንድ ኢንቨስት ማድረግ አስተማማኝ በሆነ እጅ ገንዘብ እንደማስቀመጥ ይቆጠራል::ምንጊዜም ገንዘብህን ከነወለዱ እንደምታገኝ ጥርጣሬ ልገባህ አይችልም ማለት ነው::

የቦንድ አሰራር በአገራችንም የተለመደ ነው:: በተለያዩ ጊዜያት የሚሸጥ የመንግሥት ግ/ቤት ሰነድ፣የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ያዘጋጀው ኮርፖሬት ቦንድ እና በአሁኑ ጊዜ በአገር ውስጥና በውጭ ለሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በመሸጥ ላይ የሚገኘው የህዳሴው ግድብ ቦንድ በዋናነት የሚጠቀሱ ሆነው በተለይ የህዳሴው ግድብ ቦንድ ኢትዮጵያዊያንን በአንድነት አስተባብሮ ከዳር እስከ ዳር ያንቀሳቀሰና ያሳተፈ ነው ማለት ይቻላል::

## የህዳሴ ግድብ ቦንድ ዓላማና ጥቅሙ

በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ግብርና መር የሆነውን ኢኮኖሚያችንን በኢንዱስትሪ ሊመራ ወደሚችልበት ደረጃ ለማሸጋገር የወሳኝ ምዕራፍ ተግባር ነው:: ለዚህ ዕቅድ ስኬት የኤልክትሪክ ኃይል ቁልፍ ግብዓት መሆኑ ደግሞ ግልፅ ነው:: ከኤሌክትሪክ ኃይል አንፃር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የኃይል ማመንጨ ት አቅማችንን አሁን ካለበ ት 2,000 ሜጋዋት ወደ 10,000 ሜጋዋት በማድረስ ከራሳችን አልፈን ለጎረቤቶቻችንም ለመትረፍ በሚያስችለን ደረጃ የተቃኘ ነው:: ለዚህ ዕቅድ ስኬት ወሳኝ ድርሻ ያለው በዓባይ ወንዝ ላይ እየተገነባ የሚገኘው 5250 ሜጋ ዋት ኃይል የማመንጨት አቅም ያለው የህዳሴ ግድብ ፕሮጀክ ት ነው:: የህዳሴው ግድብ ፕሮጀክት ወደ 80 ቢሊዮን የሚጠጋ ብር ይፈጃል ተብሎ ይገመታል:: ለግድቡ የሚያስፈልገውን ወጪ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ መንግሥትና ህዝብ አቅም ለመሸፈን መንግሥት ወስኖ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል::

ለህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት የሚውል ገንዘብ ለመሰብሰብ መንግስት ያስቀመጠው አቅጣጫ በአገር ውስጥና በውጭ ከሚኖሩ ኢት ዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በቦንድ መበደር፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን በራሳቸው ተነሳሽነት በስጦታ ከሚለግሱት ገንዘብና መንግሥት ከሚመድበው ዓመታዊ በጀት ነው ::ስለዚህ መንግሥት ይህንን በአገሪቱ ታሪክ ከፍተኛ የሆነ ወጪ ለመሸፈን በየዓመቱ ከሚመድበው በጀት በተጨማሪ ቦንድ በመሸጥና በበጎ ፈቃድ የሚሰጥ የድጋፍ ገንዘብ በማሰባሰብ ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል::

ቦንዱ ህዝብን በአገሩ ልማት በቀጥታ በባለቤትነት የማሳተፍ ዓላማ አለው:: ውጤቱም በራስ አቅም በታሰበው መሰረት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ የማድረግ ጥቅም ይኖረዋል:: ይህንን ስናሳካ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዕርዳታና ብድር ካላገኙ ወንዙ የእኛ ብቻ ይሆናል ብለው በቀብፀ ተስፋ የሚጠባበቁ ባላንጦቻችንንም እናሳፍራለን::

በሌላ በኩል ቦንድ መግዛት ኢትዮጵያውያን ለዚህ ታሪካዊ ፕሮጀክት ገንዘባቸውን በማበደር ለአገራቸው ልማት የድርሻቸውን የሚያበረክቱበትን ዕድል ይፈጥርላቸዋል :: በመሆኑም ለዚህ ፕሮጀክት ማበደር በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንደሚባለው አንድም ገንዘብን በአስተማማኝ እጅ በማስቀመጥ ከተሻለ ወለድ ጋር የጊዜ ገደቡ ሲደርስ መልሶ መጠቀም ሲሆን በሌላ በኩል አገራችን ለዘመናት አንገት ካስደፋት ድህነት ለመላቀቅ በሚታደርገው ትግል ተሳታፊ በመሆን የዜግነት ግዴታ በመወጣት የሕሊና እርካታ ማግኘት ይሆናል::

1. <u>የቦንዱ ይዘትና ዓይነት</u>
   - የቦንዱ ዓይነት -- ኮርፖሬት ቦንድ
   - ቦንዱን ያዘጋጀው--- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን
   - ወ ኪል ---- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
   - የቦንዱ ስም ----- የታላቁ ህዳሴ ግድብ ቦንድ
   - ክፍያ የሚፈጸምባቸው የገንዘብ ዓይነቶች ------ አሜሪካን ዶላር
   - ዝቅተኛው የቦንድ ዋጋ 50 የአሜሪካን ዶላር ሆኖ ባለ 100፣ 300፣ 500፣ 1,000፣ 3,000፣5,000 እና 10,000 ኩፖኖች አሉት::
   - የቦንዱ የጊዜ ገደብ ባለ5 ዓመት ባለ6 ዓመት ፣ባለ 7 ዓመት እና ባለ 10 ዓመት ናቸው::
   - በቦንዱ የቆይታ ጊዜ የሚከፈለው የወለድ መጠን የሚለያይ ሆኖ ለባለ5 ዓመት LIBOR+1.25% ለባለ 6 ወይም 7 ዓመት LIBOR+1.5% እና ባለ 10 ዓመት LIBOR+2% ወለድ በየ6 ወሩ እየተሰላ ይከፈላል::

2. <u>የቦንድ መግዢያ አማራጭ መንገዶች</u>

- በሚኖሩበት አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት በአካል በመቅረብ መግዛት ፤
- ቦንዱን የሚገዙበትን የገንዘብ መጠን በ ***Money Order*** በመላክ ወይም በ **BMO** ባንክ በተከፈተ ው ሂሳብ ቁጥር 2974-4799-028 በማስገባት ዲፖሲት ስሊፑን በፋክስ ለቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት በመላክ ኩፖን መውሰድ፤
- የክፍያውን ገንዘብ በባንክ በኩል በስዊፍት/SWIFT/ CODE;CBETETTAA/ የመላኪያ ዜዴ በመጠቀም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለዚሁ በተከፈተ ሂሳብ ቁጥር 02702-5577-4200 በማስተላለፍ የተላከበትን ማስረጃ ለቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት ሲልኩ ባስተላለፉት የገንዘብ መጠን ኩፖን ይላክላቸዋል::

3. <u>የዋናው ቦንድና ወለድ አከፋፈል</u>

- የቦንድ ዋና ገንዘብ የሚከፈለው የቆይታ ጊዜው ሲያበቃ ሆኖ ወለድ በየ6ወሩ በገዢዎች ምርጫ መሠረት :-

- በግንባር በመቅረብ ወይም በህጋዊ ወኪል በኩል ፤

- በውጭ ምንዛሪ በሀገር ውስጥ ባንኮች በሚከፍቱት ሂሣብ ገቢ በማድረግ፤

- ገዢው ወደሚኖርበት ውጭ ሀገር በማስተላለፍ፤

- ሌላ ተጨማሪ ቦንድ ለመግዛት ፤

- ከውጭ ለሚያስገቡት ዕቃዎች ክፍያ ለመፈፀም ሊጠቀሙበት ይችላሉ::

- **የቦንዱ የጊዜ ገደብ ሲደርስ የቦንዱ ዋጋ በገዢው ምርጫ መሠረት:-**
  - በገዛበት የውጭ ምንዛሪ ሲከፈለው
  - በውጭ በሚከፍተው ሂሳብ ገቢ ሲደረግለት
  - ሌላ ተጨማሪ ቦንድ ሲገዛበት ወይም

- ከውጭ አገር ለሚያስገባቸው ዕቃዎች ክፍያ ለመፈፀም ወዘተ... ሊጠቀምበት ይችላል::

4. <u>የቦንዱ ሕጋዊ ንብረትነትና የገዢው መብቶች</u>

የህዳሴውን ግድብ ቦንድ የገዛ ሰው ቦንዱን:-

-ከባንክ ብድር ለማግኘት በዋስትና ማስያዝ፤እና

-ለሚፈልገው ሰው በስጦታ ወይም በውርስ ማስተላለፍ ይችላል::

ለማጠቃለል ቦንድ መግዛት ለአገርና ለወገን ከሚሠጠው ጥቅም በተጨማሪ ገዢው በአሁኑ ጊዜ የውጭ አገር ባንኮች ከሚሰጡት ወለድ ከእጥፍ በላይ ወለድ የሚከፈለው በመሆኑ የበለጠ ተጠቃሚ ይሆናል::


**የኢፌዲሪ ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት**

**<u>ቶሮንቶ</u>**

ስልክ:- 416 482 6637

ፋክስ:- 416 486 9175

ኢሜል:- info@ethioconsulatecanada.com